የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20[th] Year No. 32
ADDIS ABABA 28[th] April, 2014

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፯/፳፻፮ ዓ.ም

የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ....ገጽ ፯ሺ፫፻፹፪

CONTENTS

Regulation No. 307/2014

Sesame and White Pea Beans Transaction Council of Ministers (Amendment) Regulation …. Page 7382

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፯/፳፻፮

## የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፳፻፫ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፴፩(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፫፻፯/፳፻፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ማሻሻያ**

የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፰/፪ሺ፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና (፱) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና (፱) ተተክተዋል፡-

"፰/ 'ማዘጋጀት' ማለት የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርትን አበጥሮና ከባዕድ ነገር አፅድቶ ለገበያ ለማቅረብ ማስናዳት ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 307/2014.

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND THE SESAME AND WHITE PEA BEANS TRANSACTION REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 31(1) of the Ethiopian Commodity Exchange Proclamation 550/2007(as amended).

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Sesame and White Pea Beans Transaction Council of Ministers (Amendment) Regulation No. 307/2014".

2. **Amendment**

The Sesame and White Pea Beans Transaction Council of Ministers Regulation No. 178/2010 is amended as follows:

1/ sub-article (8) and (9) of Article 2 of the Regulation are deleted and replaced with the following new sub-article (8) and (9):

"8/ 'preparation' means supplying sesame or white pea beans for market after winnowing and making it clean from any foreign materials;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፱/ 'አግባብ ያለው የክልል አካል' ማለት ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤"

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ተተክቷል፡-

"፲፪/ 'ሚኒስቴር' ወይም 'ሚኒስትር' ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤"

፫/ በደንቡ አንቀጽ ፪ ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) እና (፲፮) ተጨምረዋል፡-

"፲፭/ 'አቀናባሪ' ማለት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄን ኢንዱስትሪ ተጠቅሞ በመፈተግ፣ በመቁላት ወይም ጣህና፣ ሐለዋ ወይም የምግብ ዘይት በማምረት ወይም ሌሎች መሰል የኢንዱስትሪ ምርት በማምረት ለገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤

"፲፮/ 'አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት' ማለት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለማዘጋጀት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ ወይም ለማቀናበር ወይም ለመሰል ተግባራት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤"

፬/ የደንቡ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩/ በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በአምራቾችና በአቅራቢዎች ወይም በአምራቾችና በአቀናባሪዎች መካከል ብቻ የሚከናወን ይሆናል፡፡"

፭/ የደንቡ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩/ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በአምራቾች ወይም በአቅራቢዎች እና

9/ 'appropriate regional organ' means the regional organ that is legally empowered to administer trade activities;"

2/ sub-article (12) of Article 2 of the Regulation is deleted and replaced with the following new sub-article (12):

"12/ 'Ministry' or 'Minister' means the Ministry or Minister of Trade, respectively;"

3/ the following new sub-article (15) and (16) are added under Article 2 of the Regulation:

"15/ 'processor' means any person who scrubs or roasts sesame or white pea beans using processing industry or produces *tahna* or *halewa* or edible oil or other similar industry products and supply to the market;

16/ 'appropriate sector office' means an organ that is empowered to issue certificate of competence for any person to prepare, store, transport or process or to carry out other related activities in relation with sesame or white pea beans transaction;"

4/ sub-article (1) of Article 3 of the Regulation is deleted and replaced with the following new sub-article (1):

"1/ The transaction of sesame or white pea beans at primary transaction centers shall be carried out only between producers and suppliers or producers and processors."

5/ sub-article (1) of Article 4 of the Regulation is deleted and replaced with the following new sub-article (1):

"1/ The transaction of sesame or white pea beans at the Ethiopian Commodity Exchange shall be carried out only between producers or suppliers and

በላኪዎች ወይም በአቀናባሪዎች መካከል ብቻ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ስርዓት መሠረት የሚከናወን ይሆናል፡፡"

፮/ በደንቡ አንቀጽ ፮(፪)፣ ፯(፪) እና ፰(፬) ውስጥ "በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን" በሚል የተገለጸው ተሠርዞ "በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል" በሚል ተተክቷል፡፡

፯/ ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ በደንቡ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "ሚኒስቴር" ወይም "አግባብ ያለው የክልል አካል" በሚል የተገለጸው ተሠርዞ "አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት" በሚለው ተተክቷል፡፡

፰/ የደንቡ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩/ ወደ ውጭ አገር የሚልከውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም በአገሪቱ የጥራት ደረጃ ያልወጣለት ከሆነ በገዥው መሥፈርት መሠረት የማዘጋጀት ወይም የማቀነባበር፤

፱/ የደንቡ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፭) የነበረው ንዑስ አንቀጽ (፯) ሆኖ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ተጨምረዋል፡-

"፭/ ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመግዛት፤

፮/ ተረፈ ምርትን ወይም ብጣሪን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ አቅርቦ የመሸጥ፤"

፲/ የደንቡ አንቀጽ ፲፮ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፮ ተተክቷል፡-

"፲፮. <u>የአቀናባሪ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም አቀናባሪ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

፩/ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዛውን ምርት ፈትጎ ወይም ቆልቶ ወይም ጣህና፣

exporters or processors based on the Ethiopian Commodity Exchange rules."

6/ the expression "Ethiopian Quality and Standardization Authority" appearing in Article 6(2), 7(2) and 8(4) of the Regulation is deleted and replaced with the expression "legally empowered organ".

7/ the expression "Ministry" or "appropriate regional organ" appearing anywhere in the Regulation in connection with certificate of competence is deleted and replaced with "appropriate sector office".

8/ sub-article (1) of Article 15 of the Regulation is deleted and replaced with the following new sub-article (1):

"1/ prepare or process export sesame or white pea beans based on the quality standard of the country or, if there is no Ethiopian quality standard already set, based on the standard requirement of the buyer;"

9/ sub-article (5) of Article 15 of the Regulation is renumbered as sub-article (7) and the following new sub-article (5) and (6) are added:

"5/ buy sesame or white pea beans only at the Ethiopian Commodity Exchange;

6/ resell by-products or rejects at the Ethiopian Commodity Exchange;"

10/ Article 16 of the Regulation is deleted and replaced with the following new Article 16:

"16. **<u>Obligations of Processors</u>**

Any processor shall:

1/ scrub or roast sesame or white pea beans bought at primary transaction centers or process *tahna*, *halewa*, edible oil or other

ሐለዋ፣ የምግብ ዘይት ወይም መሰል ኢንዱስትሪያዊ ምርት አቀናብሮ ለገበያ የማቅረብ፤

similar industrial product and supply to market;

፪/ ተረፈ ምርትን ወይም ብጣሪን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ አቅርቦ የመሸጥ፤

2/ resell by-products and rejects at the Ethiopian Commodity Exchange;

፫/ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አዘጋጅቶ ብቻ ለገበያ ያለማቅረብ፤

3/ not only prepare and supply to the market sesame or white pea beans bought at primary transaction centers;

፬/ ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ዳግም ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያለማቅረብ፤

4/ not introduce for re-trade to the Ethiopian Commodity Exchange sesame or white pea beans bought at primary transaction centers or at the Ethiopian Commodity Exchange;

፭/ ስለሚያቀናብረው ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ሲጠየቅ ማንኛውንም መረጃ የማቅረብና ናሙና የመስጠት።"

5/ when requested, provide any information regarding the sesame or white pea beans that is being processed and give sample thereof."

፲፩/ የደንቡ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል፦

11/ sub-article (4) of Article 17 of the Regulation is deleted and replaced with the following new sub-article (4):

"፬/ ወደ ውጭ አገር የሚላክን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም በአገሪቱ የጥራት ደረጃ ያልወጣለት በሆነ ጊዜ በገዥው መሥፈርት መሠረት የማዘጋጀት፤"

"4/ prepare export sesame or white pea beans based on the quality standard of the country or, if there is no Ethiopian quality standard already set, based on the standard requirement of the buyer."

## ፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

## 3. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publicatoin in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

**Done at Addis Ababa, this 28th day of April, 2014.**

ኃይለማርያም ደሳለኝ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት